# የሠላም ገበሬ

የሰላምን ዘር ኮትኩተህ አብቅለው፤
አረም እንዳይውጠው ተንከባክበህ ያዘው።

ያልዘራኸው ዘር እንደማይበቅል አውቀህ፤
ችግኝህን አሳድግ ማዳበሪያው ሆነህ።

የሰላም ችግኝህ ያድግና ያብባል፤
ለሰላም መስፋፋት ሌት ተቀን ይጥራል።

ሰላም ለፍርድ ስትቀርብ የሰላም ጠበቃ፤
እውከት መንገድ ያጣል እጅግ ያፈራል በቃ

ሰላም ስትታሰር እሱ ነው ፈችዋ፤
ሰላም ስትታወር ዓይነ ብረሃንዋ፤
ሰላም ስትቆስል ጠጋኝዋ መሐንዲስ፤
እሱ ነው የሰላምን ሕይወት በጊዜ የሚያድስ።

ሰላምን ለራበው ሰላምን ይመግባል፤
የሰላምን ችቦ ለሁሉ ያበራል፤
አንተን ብቻ ሳይሆን ዓለምን ያኮራል።

ከ ኒኒ ለገሰ